# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች የአስተዳደር መመሪያ ቁጥር 971/2015

Administrative Directive for Academic Technical Assistants of Higher Education Institutions Instruction
(Directive No. 971/2023)

ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education

ግንቦት 1፥ 2015

በትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ በተሻሻለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የትምህርት ጥራት ማስጠበቅ ቀዳሚው ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ እየተሰራ ስለሚገኝ፤

ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃን ለማፍራት በትምህርት ተቋማት የሚሰጠው የተግባር ትምህርት በተገቢው ሁኔታ መሰጠቱ እጅግ አስፈላጊ ስለሚሆን፤

የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች ለዚሁ ብቁ ምሩቃን የማፍራት ሥራች የላቀ ሚና ስለሚጫወት የሥራ ሁኔታቸው ማለትም መብትና ግደታውን የሥራ ሚናቸውንና ተግባራ ያላቸውነ ጥቅማ ጥቅም መደንገግ በማስፈለጉ፤

የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን ተግባርና ኃላፊነት እና ጥቅማ ጥቅምን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 534/2015 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

Recognizing the vital necessity of ensuring that educational institutions deliver practical education under optimal conditions to foster the emergence of competent and competitive graduates,

In light of the paramount significance attributed to upholding educational quality within the revised education and training policy outlined in the education and training roadmap,

Acknowledging the pivotal role played by academic technical assistants in the production of competent graduates, necessitating the appropriate regulation of their working conditions encompassing their rights and obligations,

This Regulation is issued by the ministry of education In accordance with the provisions stipulated in Article 7, sub-article 1 of The Roles, Responsibilities and other benefits of Academic Technical Assistants working in Public Governmental Higher Education Institution and Teaching Hospitals Council of Ministers Regulation No.534/2023.

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 971/2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

**2. ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ሥራ ላይ የዋሉ የቁልፍ ቃላት ፍች ለአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች በወጣው ደንብ ቁጥር 534/2015 አንቀጽ 2 የተገለጹትን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች ቅጥር፣ አስተዳደር፣ ደረጃ እድገት፣ መብትና ግዴታ እንዲሁም

**4. መርህ**

የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች አስተዳደርና ጥቅማ ጥቅም በሚከተሉት መርሆች ይመራል፡፡

ሀ/ ተጠቃሚነትና ፍትሃዊነት

ለ/ ህጋዊነት

ሐ/ ለእኩል ሥራ እኩል ተከፋይነትና ተሳፎትፎ

መ/ ግልጽነት እና

ሠ/ ውጤታማነት

## Part one

## General Provisions

**1. Short Title**

This directive shall henceforth be referenced as the Administrative Directive for Academic Technical Assistants in Government-Operated Institutions of Higher Education, herein referred to as Directive No. 971/2023.

**2. Definition**

The explication of pivotal terminology employed in this compendium shall incorporate the definitions as explicitly outlined in Article 2 of Regulation No. 534/2015 concerning Academic Technical Assistants.

**3. Scope of Applicability**

This directive shall extend its purview over government-operated institutions of higher education that bear the onus of accountability to the Ministry of Education with regard to matters concerning the recruitment, administration, advancement, entitlements and obligations, as well as benefits bestowed upon academic technical assistants.

## ክፍል ሁለት

## መብቶችና ግዴታዎች

5. መብቶች

በደንብ 354/2015 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.1 የተደነገጉ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣

1. ለአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች ከሙያቸው ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል ሲገኝ በውድድር ሥርዓት ተወዳድሮ የማግኘት፣
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም የአጭር ጊዜ (እስከ ሶስት ወር የሚወስድ) እና የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል (ከስድስት ወር በላይ የሚወስዱ) ሥልጠናዎች በተቋሙ ፍላጎት መሰረት ተወዳድረው የማግኘት፤

3. ተቋሙ የሚፈልገው የትምህርት መስክ መሰረት ባደረገ መልኩ በሃር ውስጥና በውጭ ሀገር በግል ጥረት በሚገኝ የአጭር (እስከ 6 ወራት) እና የረጅም (ሁለተኛ እና

**4. Guiding Principles**

The administration and allocation of academic technical assistants shall be governed by the ensuing principles:

A/ Usability and Equitability

B/ Legality

C/ Equal Compensation and Engagement for Equal Labor

D/ Transparency

E/ Efficiency

## Part two

## Rights and duties

**5. Rights**

Subject to the entitlements prescribed in Rule 354/2015, Article 6, Sub-article 6.1:

1. The entitlement to avail oneself of short-term and long-term training opportunities within the country and abroad, specifically tailored to the professional domain of academic technical assistants, through a competitive framework.
2. All short-term (up to six months) and long-term (exceeding six months) educational programs shall be competitively determined, contingent upon the requirements of the institution, as stipulated in Sub-article 1 above.

ሶስተኛ ዲግሪ) የትምህርት ዕድል የመጠቀም፣

4. የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች በትምህርት ላይ እያሉ የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅም በተመለከተ ለመምህራን በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተጠቃሚ የመሆን፣

5. የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ መደበኛ ባልሆኑት የመማር ማስተማር፣የጥናትና ምርምር፣ የማህበረሰብ ጉድኝት ሥራዎች ሲሳተፍ በተቋሙ የውስጥ መመሪያ መሰረት የመስተናገድ፣

6. በተቋሙ በሚገኙ የትምህርት ክፍሎች የመምህር ፍላጎት መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች እርስ በእርስ ተወዳድረው ወደ መምህርነት የማደግ፣

7. የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ወደ መምህርነት ከተሸጋገሩ በኋላ በህግ አግባብ ለአካዳሚክ ደረጃው የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም የማግኘት፣

3. The utilization of short-term (up to six months) and long-term (second and third degree) educational prospects, both domestic and international, aligned with the academic discipline as desired by the institution.

4. The receipt of educational benefits, as per the procedure established for instructors, to which academic technical assistants are entitled during their educational pursuits.

5. In the event of academic technical assistants engaging in non-formal educational, research, and community service activities, they shall be accorded treatment in accordance with the internal guidelines of the institution.

6. Following the verification of a need for instructors within the institution's departments, academic technical assistants shall compete amongst themselves for the opportunity to become instructors.

8. የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ወደ መምህርነት ከተሸጋገሩ በኋላ በህግ አግባብ ለአካዳሚክ ደረጃው የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም የማግኘት፣

9. የከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ የዓመት ዕረፍትን በተመለከተ የአካዳሚክ ካሌንደሩን መሰረት ያደረገ ዕረፍት የማግኘት፣

6 <u>ግደታዎች</u>

በደንብ 354/2015 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.1 የተደነገጉ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ

1. ወደ መምህርነት ለመዛወር በቺፍ ቴክኒካል ረዳት I የቆይታ ጊዜውን ሁለት ዓመት የአገልግሎት ጊዜውን ያጠናቀቀ፣ ለጊዜው የተቀመጠውን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ድግሪ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን የቅጥር መስፈርት/ውጤት የማሟላት፣

2. ወደ መምህርነት ለመወዳደር ያለፉት የሶስት ተከታታይ ዓመታት የስራ አፈጻጸም የግምገማ ውጤት ከፍተኛ እና ከዚያ በላይ የማምጣት፤

7 Academic technical assistants, upon fulfilling the established criteria, shall be entitled to the benefits legally granted for their academic status subsequent to transitioning into the role of instructors.

8 The entitlement to annual leave for academic technical assistants of higher education, based on the academic calendar of the university.

**6. <u>Obligations</u>**

Pursuant to the obligations delineated in Rule 354/2015, Article 6, Sub-article 6.1, the technical assistant is bound by the following obligations:

1. Serve a tenure of two years as the Chief Technical Assistant and fulfill the contemporary recruitment criteria in both the first and second degrees, as prerequisites for promotion to the position of an instructor.
2. Attain promotion to the position of an instructor based on the performance evaluation outcomes of the past three consecutive years, ranking as high and above.

3. በቆይታ ጊዜው በተቋሙ የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርድ የሌለበትና ወይንም የዲሲፕሊን ቅጣት ካለበትም የቅጣቱን የቆይታ ጊዜ ያጠናቀቀ፤
4. ለተግባር ትምህርት የሚያገለግሉ የተለያዩ አይነት ማንዋሎችን በጥራት አዘጋጅቶ ተገቢውን ግንዛቤ በመፍጠር ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤ የተዘጋጁ ማኑዋሎችንም የመገምገም ብሎም ማስተካከያ የመስጠት፤
5. ለተማሪዎች የመመረቂያ እና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመስራት እንደ መነሻ ሃሳብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ናሙና ፕሮጀክቶችን የመስራትና ግንዛቤ ፈጥሮ ተማሪዎች እንድጠቀሙበት የማድረግ፤
6. የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና ተቋሙ የሚመራባቸውን እሴቶች የማክበር፤ የመተግበርና በሙያዊ ስነ ምግባርና አግባብነት የመወጣት፤

3. Maintain a disciplinary record free from infractions during the tenure at the institution, or if subjected to disciplinary sanctions, duly serve the duration of the imposed penalty.
4. Prepare diverse manuals that facilitate the provision of practical, high-quality education and ensure their utilization through the creation of adequate awareness among students.
5. Develop sample projects that can serve as starting points for students engaged in thesis and other academic projects, fostering awareness and encouraging their utilization.
6. Adhere to and uphold the objectives and values of higher education that guide the institution, conducting oneself with professional ethics and propriety.

7 የተለያዩ የላብራቶሪ /የመስክ፣ የወርክ ሾፕ መሳሪያዎችን ደህንነት መጠበቅ፤ ማደራጀት፣ ሲበላሹ መጠገን እና ለመጠገን ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታው አካል ሪፖርት በማድረግ እና አፈጸጸሙን በመከታተል ብቃታቸውን አረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣

8 ከሌሎች የሚመለከታቸው መምህራን እና ተመራማሪዎች ጋር በመተባበር የተለያዩ ላብራቶሪ (ወርክ ሾፕ ) እንዲደራጁ የማድረግ፤

9 ከቤተ ሙከራ/ወርክ ሾፕ ጋር በተያያዘ በአካባቢ ላይ ከሚደርሱ ተጽዕኖ በጸዳ ሁኔታ የሚሰራበትን የተለያየ ዘዴዎችን በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋጽኦ የማበርከት፤

10 የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያዎች በተግባር ትምህርት በሚከናወን የተማሪ ግምገማ ላይ የመሳተፍና ከ20 በመቶ ውጤት የመስጠት ላፊነት ሲሆን የመጨረሻውን ውጤት የሚሰጠው የኮርሱ ባለቤት መምህሩ ይሆናል፡፡

7 Safeguard a range of laboratory and workshop equipment, organizing and undertaking repairs when damage occurs, and promptly reporting to the appropriate body in instances where repair lies beyond one's capacity, monitoring their implementation, ensuring their efficiency, and facilitating their usability.

8 Collaborate with relevant stakeholders and researchers to organize various laboratories and workshops

9 Contribute to the implementation of diverse methodologies conducive to a free and open environment within laboratories and workshops.

10 Engage in the assessment process of students during practical education, whereby technical assistants evaluate 20% of the course activities while the remaining 80% falls under the purview of the principal instructor.

11 በቀን 8 ስዓት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ተገኝቶ የመስራት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በላብራቶሪ / ወርክሾፕ ከተማሪዎች ጋር የሚቆዩበት ጊዜ አንድ ስዓት የዝግጅት ጊዜ በሚል ስሌት ሳምንታዊ የስራ ጫና 20 ስዓት የመስራት፣

12 ከቤተ- ሙከራ/ከመስክ ስራ የሚገኙ ማንኛውንም የልኬት ወይም የምልከታ ውጤቶች ትክክል መሆናቸውን የማረጋገጥና ውጤቱን ለሚፈልጉ አካላት መረጃ የመስጠት፤

13 በተቋሙ ያሉት የምርምር ውጤቶች በተቋሙ ተመራማሪዎች የሚገኙ የምርምር ውጤቶች(ቴክኖሎጂዎች) ከተመራማሪዎች ጋር በመቀናጀትና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ወደ ማህብረሰቡ እንዲወርዱ የማገዝ፤

14 ከትምህርት ክፍሎች፣ ኮሌጆች፣ ፋካሊቲዎች፣ ማስተማሪያ ሆስፒታሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመሆን የማቀድና በተቋሙ ተልዕኮ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ንቁ ተሳትፎ የማድረግ፤

11 Dedicate a weekly commitment of 20 hours, including one hour per day reserved for laboratory and workshop preparation with students, while fulfilling the obligation to be present and work for a total of 8 hours each day.

12 Verify the accuracy of measurement or observation results derived from laboratory and field work, providing information to interested parties.

13 Facilitate the dissemination of the institute's research findings and technologies, coordinated with researchers and offering professional support, thus enabling their practical implementation within society

14 Actively participate in the planning and evaluation processes of the institution's mission, collaborating with educational departments, colleges, faculties, teaching hospitals, and research centers

7. **<u>የተሻሩ ህጎች</u>**

የአካዳሚክ ቴክኒካል ረዳት ባለሙያዎችን በተመለከተ ከአሁን በፊት የተላለፉ ሰርኩላሮች እና መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**7. <u>Abrogated Statutes</u>**

Any prior circulars and instructions that have been promulgated concerning Academic Technical Assistants shall hold no bearing or applicability to this present directive.

8. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ጥናትን መሰረት አድርጎና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚቀርብ ግብዓት መሰረት ሚኒስቴሩ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**8. <u>Directive Enhancement</u>**

The Ministry reserves the right to amend and enhance the directive through the incorporation of research findings and feedback received from institutions of higher education.

9. **<u>ማጽኛ ድንጋጌ</u>**

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ተፈርሞ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ ገጽ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**9. <u>Effective Date</u>**

This directive will come into force on the day it is signed by the Minister and uploaded on the ministry of justice website.

ብርሀኑ ነጋ /ፕሮፌሰር/

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

ግንቦት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

Brhanu Nega /Professor/

Minister of Education

May 2023

Addis Ababa